ልደታ ካቶሊክ ካቴድራል ት/ቤት ሚያዝያ 19 / 2012 ዓ.ም
የትምህርት ዓይነት ሂሳብ
3ኛ ክፍለ ጊዜ ሂሳብ ትምህርት የትምህርት
መካካሻ ጥያቄዎች
ክፍል 2ኛ

## ምዕራፍ ስድስት

### ክብ / /

በመጀመሪያ ክብ ማለት ምን ማለት ነው ?

ክብ ማለት አንድ ሙሉ ዙር ማለት ነው ::

ክብ በምስል መልክ የሚከተለውን ይመስላል ::




ይህ አንድ ሙሉ ክብ ነው ::

እነዚህ ሀ ለ ሐ መ ፊደሎች ሲገናኙ አንድ ሙሉ ዙር / ክብ / ይሰራሉ :: ማንኛውም ክብ የመለያያ ነጥብ የለውም :: ለዚሁ የጆኦሜትሪ ምስል መነሻው ነጥብ ነው ::

በተጨማሪም ክብ ውስጥ መሀል ለመሀል ክቡን እኩል በእኩል የሚከተለው መስመር ዲያሜትር ይባላል ::

የዲያሜትር ግማሽ ደግሞ ሬዲያስ ይባላል ::

የሬዲያስ ሁለት እጥፍ ከሆነ ደግሞ ዲያሜትር ይሆናል ::




በዚሁ ክብ የተመለከቱት ነጥቦች ዘ፣ ፈ ፣ ጠ ፣ የ ፣ ነ እና መ ሌሎቹም ነጥቦች ከመሀል ነጥብ "ወ" እኩል ርቀት አላቸው :: በተጨማሪም ሬዲያስ ተብለው ይጠራሉ ::

## የሚከተሉትን ምስሎች ስማቸው እንመለከታለን ::

1.  ሬክታንግል

2.  ማንቆርቆሪያ / ኮን /

3.  ክብ

4.  ሲሊንደር

5.  ካሬ

6.  ጎነ ሶስት ምስል / ትሪያንግ

ከላይ ያሉትን ምስሎች እንደተመለከትናቸው ስማቸውን ከተረዳን በኋላ ጥቅቶች ደግሞ የሁለት ነገሮች ውህዶች ናቸው ::

<u>ለምሳሌ</u>

1. የዘይት መቅጃ ማንቆርቆሪያ ክብናየክብ ክፋይ ነው ::
2. ሲሊንደር ክብ እና የሬክታንግል ውህድ ነው ::

## <u>1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶ ቦታውን ሙላ</u>

1. የዲያሜትር ግማሽ _______________ ይባላል ::

2. የሬክታንግል እጥፍ _______________ ይባላል ::

3. በአንድ ሙሉ ክብ ውስጥ ክቡን መሀልለ መሀል እኩል የሚከፍለው መስመር_______________ ይባላል ::

4. _______________ የመለያያ ነጥብ የለውም ::

5. ለማንኛውም የክቡ ምስል መነሻው ከ _______________ ነው ::

## <u>2/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ</u>

_______ 1. ነጥብ መሰረታዊ የማንኛውም የጂኦሜትሪ ምስል መነሻ ነው ::

_______2. ማንኛውም ጎነ አራት ምስል ካሬ መሆን ይችላል ::

_______3. ጎነ ሶስት ምስል አራት የመለያያ ነጥቦች አሉት ::

_______4. ውስን ቀጥታ መስመሮች ቀጥታ መስመሮች መሆን ይችላሉ ::

_______5. በጎነ አራት ምስል ውስጥ አራት ውስን ቀጥታ መስመሮች ይገኛሉ ::

_______6. ካሬ እና ሬክታንግል እኩል ርዝመት እና ወርድ አላቸው ::

_______7. መንቆራቆሪያ / ኮን / ክብ እና የክብ ክፋይ ነው ::

_______8. የሲሊንደር ምስል ከስር እና ከላይ ክብ ነው ::

## 3. ትክክለኛውን መልስ ምረጥ

_______1. ከሚከተሉት ውስጥ ሁለት ተቃራኒ ጎኖቹ እኩል ርዝመት አላቸው ::

ሀ. ክብ ለ. ጎነ ሶስት ሐ. ሬክታንግል መ. መልስ የለውም

_______2. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የመለያያ ነጥብ የለውም ::

ሀ. ጎነ አራት ለ. ክብ ሐ. ጎነ አምስት መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

_______3. ለማስተማሪያ የሚያገለግለን የጥቁር ሴሌዳ ቅርጽ / ምስል / የሚመደበው ከየትኛው ጋር ነው ?

ሀ. ከጎነ አራት ለ. ከጎነ ሶስት ሐ. ከክብ መ. መልስ የለውም

## 4. የሚከተሉትን ምስሎች በመመልከት በባዶ ቦታው ላይ ስማቸውን ጻፍ

1.  _______________

2.  _______________

3. 

4. 

5.  _______________

6. 

___________

___________

## 5/ ለሚከተሉትን ጥያቄወዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. ጎነ ሶስት ምስል ለመስራት ስንት ውስን ቀጥታ መስመሮች ያስፈልጋል ?

   ___________

2. የዘይት መቅጃ ማንቆርቆሪያ የምንኛ የምን ውህድ ነው ? ___________
3. አራቱንም ጎኖቹ እኩል ርዝመት ያለው ጎ አራት ምስል ምን ይባላል ?

   ___________

4. የሲሊንደር ቅርጽ የምን ውህድ ነው ? ___________
5. በጎነ አራት ምስል ውስጥ ስንት የመለያያ ነጥቦች አሉት ? ___________

**_መስታወሻ፡-_ ይህ ወረቀት ግንቦት 3 ተመላሽ ሆኖ በመምህራን ይታረማል ፡፡**